የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስራ አንደኛ ዓመት ቁጥር 61

ሠመራ ሕዳር -----ቀን 2003 ዓ.ም.

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th year No.61

samara--November/2012

ማውጫ

የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ.... ገጽ 1

አዋጅ ቁ 61/2 ዐዐ 3 ዓ.ም.

የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

መግቢያ፣

አፋር ክልል ህዝብ አርብቶ አደር እንደመሆኑ ከተፈጥሮ ሃብት ቀጥተኛ ተጠቃሚ በመሆኑ'በዚህም ለአካባቢ እንክብካቤ እና ጥበቃ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ በክልሉ መንግስት በመታመኑ'

በክልሉ በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ልዩልዩ ጥናቶች በክልሉ የአካባቢ ብክለት እየጨመረ መምጣቱና የመሬት ውጤታማነት ከጊዜ ወደጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ መምጣቱ&በዚህም ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው የክልሉ መንግስት በቁርጠኝነት መነሳቱ'

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በክልሉ በተሻሻለው የክልሉ ህገመንግስት አንቀጽ 47(3)(ሀ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር -------2 00 3 ዓ.ም.» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡

1. #ኤጀንሲ; ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ ነው።

2. #የገጠር መሬት; ማለት ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጭ ወይም አግባብ ባለው ህግ #ከተማ# ተብሎ ለሚሰየመው ውጭ ያለ መሬት ማለት ነው።

3. #የመሬት ይዞታ; ማለት በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች ወይም በሌሎች በህግ መብት በተሰጣቸው አካላት ይዞታ ስር ያለ የገጠር መሬት ነዉ።

4. #የይዞታ መብት; ማለት ማንኛውም አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች የገጠርን መሬት በእንስሳት ዕርባታ'በእርሻ ስራና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ተግባር ለማዋል'ለማከራየትና ለቤተሰቡ አባልና ለሌሎች በህግ መብት ለተሰጣቸው ወራሾች ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን&በመሬቱ ላይ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትና ይህንንም በመሬቱ ላይ ያፈራውን ንብረት መሸጥ'መለወጥና ማውረስንም ይጨምራል።

5. #አደገኛ ነገር; ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጠር'ፈሳሽ ወይም የጋዝነት ባህሪይ ያለው ነገር ወይም ተክል'እንስሳ'ወይም ረቂቅ ህዋስ ነው።

6. #አካባቢ; ማለት በመሬት' በከባቢ አየር' በአየር ሁኔታና አየር ንብረት' በውሃ'ህያዋን' በድምጽ'በሽታ'በጣዕም'በማህበራዊ ጉዳዮች ሳይወሰን&ነተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች ያሉበት ቦታ'እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታ የሚነኩ ተስተጋብሮቻቸው ድምር ነው።

7. #ጥበቃ; ማለት የተፈጥሮ ባህሪይ እንዳይናጋ በመጠበቅና የተፈጥሮ ሀብቶች ምንጭ አቅምን በማጎልበት&የአሁኑን ትውልድ ፍላጎት የማርካቱ ሂደት የመጪውን ትውልድ ዕድል ሳያሰናክል እንዲያሟላ ማስቻል ነው።

8. #ሰው; ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለክልሉ የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ መቋቋም'ዓላማ'አደረጃጀትና ስልጣንና ተግባር</u>

3. <u>መቋቋም</u>

1. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ /ከዚህ በኃላ #ኤጀንሲ; ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

4. <u>ዓላማ</u>

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ'ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኤጀንሲ ዓላማ'

1. ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች'የሰውን በጎ ሁኔታና የአካባቢን ደህንነት በዘላቂነት ሊያራምዱ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን' ስልቶችን' ህጎችንና ደረጃዎችን ማዘጋጀትና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የሚከናወነውን ተግባር በግንባር ቀደምትነት መምራት፣

2. የክልሉ ህዝብ በመሬቱ በአግባቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ከማመቻቸት ጎን ለጎን የክልሉ መሬት ለምነቱ ተጠብቆ በዘላቂነት እንዲቆይ ማስቻል ነው።

5. ዋና መስሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ከተማ ሠመራ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ ባሉ ዞኖች፣ወረዳዎች ጽ/ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል።

6. የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር

1. ኤጀንሲው በህግ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልገውን ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል።

2. ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲውን የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ/ በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የገጠር መሬት አይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፣አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ይቆጣጠራል'

ለ/ መሬቱ በተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን የመሬቱ ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎች ማድጋቸውን ይከታተላል፣መሬታቸውን በአግባቡ ለሚይዙት የተለያዩ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል'

ሐ/ እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሳ ዘዴዎችን በመጠቀም እያንዳንዱን የመሬት ይዞታ ይመዘግባል፣በምዝገባው መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል።

መ/ የመሬት ይዞታ መብት የተሰጣቸው አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች የይዞታ መብታቸውን እንደአግባብነቱ በውርስ'በኪራይ ወይም በስጦታ የሚያስተላልፉበትን ስርዓት ያስፈጽማል'በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን በየግዜው እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል።

ሠ/ የግል ባለሃብቶች በመሬት ላይ የልማት ስራ ከመጀመራቸው በፊት የአጠቃቀም ዕቅዳቸውን እየገመገመ ያጸድቃል'የኢንቨስትመንት መሬት ሊዝ አሰራርና ተመኑን በየጊዜው እያጠና ለክልል መንግስት በማቅረብ ያስወስናል'ከባለሃብቶች ጋር ውል ይፈጽማል'በውላቸው መሰረት ተግባራዊ በማያደርጉት ላይም በህግ አግባብ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

ረ/ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በሚወሰድ እርምጃ ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ባለይዞታዎች ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ እንዲያገኙና አማራጭ የኑሮ መሰረት እንዲኖራቸው ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል።

ሰ/ የክልሉን የአካባቢ ጥበቃ'የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብነት ላላቸው አካላት ስልጠና'ምክርና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።

ሸ/ የአካባቢ ሃብቶችን አስመልክቶ የዋጋ ትመና ጥናቶች ያካሂዳል' በትመናው ውጤት መሰረት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሲነደፉ በአዋጭነት ስሌታቸው ውስጥ የአካባቢ ሃብቶች ዋጋ እንዲካተት ያደርጋል' በትግበራ ወቅት ለሚደርሰው ማናቸውም የአካባቢ ሃብት ጥፋት በሃብት ትመናው መሰረት ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈል ያደርጋል ።

ቀ/ የአካባቢ ደህንነትን ለማስከበር ስልጣን'ኃላፊነትና ተግባር በተሰጣቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተግባር ላይ የምርመራና ክትትል ስራዎችን ያከናውናል'ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡት ላይ ደግሞ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

በ/ ኤጀንሲው አላማዎችን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች በህግ የተፈቀዱ ተግባራትን ያከናውናል።

7/ <u>አቋም</u>

1. ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉትን አካላት ይኖሩታል

   ሀ/ ዋና ስራ አስኪያጅ

   ለ/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ

   ሐ/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች

2. የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስኪያጅ በክልሉ ርዕስ መስተዳድር ይሾማል ።
3. የዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕስ መስተዳድር ሲሆን የምክትል ስራ አስኪያጅ ተጠሪነት ለዋና ሥራ አስኪያጅ ይሆናል።

8/ <u>የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር፣</u>

ዋና ሥራ አስኪያጅ የኤጀንሲው ዋና የሥራ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ /6/ ሥር ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ¾¡MK<” c=y=M c`y=e IÓ ›ÖnLÃ S`J‹ S’h ›É`Ô uT>¨×¨< SS]Á Sc[ƒ ¾›?Ë”c=¨<” c^}™‹ ÃkØ^M'Áe}ÇÉ^M' Áe“w ታM::
2. ¾›?Ë”c=¨<” ¯Sታ© ¾e^ ýaÓ^U“ uËƒ Á²ÒÍM'c=ðpÉU ue^ LÃ Á¨<LM'
3. ›?Ë”c=¨< u}ðkÅKƒ uËƒ“ ýaÓ^U Sc[ƒ ¾óÃ“”e QÓ” }ŸƒKA Ñ”²w ¨ß ÁÅ`ÒM::
4. ¾›?Ë”c=¨<” ÖpLL ¾›c^` H>Åƒ'¾e^ ÓUÑT ¨<Ö?ƒ“ ›e}Á¾ƒ ›eSM¡„ KT>SKŸ}¨< ›"M ]þ`ƒ Ák`vM::
5. Ÿfe}— ¨Ñ•‹ Ò` uT>ÁÅ`Ò†¨< Ó”–<’„‹ ›?Ë”c=¨<” Ã¨¡LM::
6. K›?Ë”c=¨< e^ pMØõ“ uT>ÁeðMÓ SÖ” eM×”“ }Óv\” uŸòM ለኤጀንሲው ኃLò‹ እ“ c^}™‹ u¨<¡M“ K=Áe}LMõ Ã‹LM::
7. ሌሎች አግባብነት ያላቸውና ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል።

<u>¡õM ZYƒ</u>

<u>M¿ M¿ É”ÒÑ@‹</u>

9. በጀት

የክልሉ መንግስት የኤጀንሲውን በጀት ይመድባል።

10. የሂሳብና መዛግብት አያያዝ

1. ኤጀንሲው የተሟላና አግባብነት ያላቸው የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል
2. የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየአመቱ በክልሉ ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራል።

11. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ'ደንብ'መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ዘዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

12. ስለመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ

የገጠር መሬት አስተዳደርን በሚመለከት በተለምዶ የአርብቶ አደር'ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሲሰራቸው የነበሩ ስራዎችና በአዋጅ ቁጥር 49/2001 የተመለከቱተ መብትና ግዴታዎቸ በዚህ አዋጅ ለኤጀንሲው ተላልፈዋል።

13. Å”w“ መመሪያ የማውጣት ስልጣን

u²=I ›ªÏ Sc[ƒ

1/ ¾¡MK< Se}ÇÉ` U¡` u?ƒ ÃI” ›ªÏ KTeðçU ¾T>ÁeðMÑ< Å”x‹” K=Á¨× Ã‹LM::

2/ ኤጀንሲው u¡MK< Se}ÇÉ` U¡` u?ƒ ¾T>¨Ö< Å”x‹” ለማስፈፀም የሚያስችሉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

14.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራ ---------- **2** ዐዐ **3** ዓ.ም.

እስማኤል ዓሊ ሴሮ

የአፋር ብ/ክ/መንግስት

ርዕስ መስተዳድር